# ተው በሉልኝ!



“ሂድ ሞት ሆይ ቀማኛ፣ ክፉ፣ ልብ ኣቁስል
ራቅ! ጥፋ! ኣትምጣብኝ! እኔ ኣልወድም ለቅሶ!”
ስለው ኣይሰማኝ!
ከንዳዬ ገብቶ ጐምለል ኣለብኝ
ዘመድ፣ ኣዝማድ፣ ወዳጅ፣ ጓደኛ ይመስል
ኣንቆ ይስመኛል መልሶ፣ መላልሶ…



ሂልዳ ጐርፉ 10/04/54 – 12/22/07

ልክፍት፣ ጥልመያኮስ፣ ክፉ፣ መልከ ቁራ፣
ወንድሜን፣ እህቴን፣ ኣንድ-ባንድ ወስዱቸው፣
ኣረ ተው በሉልኝ!
ከኣልጋየ ወጥቶ፣ ሚስቴንም ደፍሮብኝ፤
ኣባቴን፣ እናቴን ሳይበቃው በተራ
እያከታተለ በልቷቸው፣ ውጧቸው…

ዳር፣ ጠረፍ ወስዳችሁ ኣጥፉት ያን ቀጣፊ፣
ይበቃሃል በሉት፣ ኣባርሩት ከቤቴ!
ዝምድናው ይቅርብኝ!
ሚስቴን ይዞ ጠፍቶ፣ ቤቴን ኣውድሞብኝ፣
ርኅራሔም የለው፣ ይህ መጥፎ፣ ሰው ኣጥፊ፣
ግን ኣልሸነፍም፣ መሪር ነው ሓሞቴ…

ገ/ኢ. ጐርፉ።